# አስደናቂው ሕፃን ።



ከጥሩነሽ ይመር

QQD
892.826
TER
----------
254,660

# አስደናቂው ሕፃን ።

## የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ
## ልደት ።

ከጥሩነሽ ይመር የተጻፈ

## ድራማ ።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
በሠላሳ ዘጠነኛው ዘመነ መንግሥት ።

አዲስ አበባ ፣ ፲፱፻፷፩ ዓ. ም.

በሴንትራል ማተሚያ ቤት ታተመ ።

ፕሬስብቴሪያን ሥነ ጽሑፍ ድርጅት ።

የመጽሐፉ መብት የተጠበቀ ነው ፤- በመጽሔት ወይም በጋዜጣ አስተያየት ለመስጠት ካልሆነ በቀር ፥ ከዚህ መጽሐፍ ማንኛውንም ክፍል ለማሳተም ወይም ለማራባት ከአሳታሚው ድርጅት የጽሑፍ ፈቃድ ያስፈልጋል ።

# ክፍል አንድ ።

## ፩ኛ ትእይንት ።

መልአኩ ገብርኤል ናዝሬት ወደምትባል ወደ ገሊላ ከተማ ፣ ከዳዊት ወገን ለሆነው ዮሴፍ ለሚባል ሰው ወደ ታጨች ወደ አንዲት ድንግል ከእግዚአብ ሔር ዘንድ ተላከ ፤ የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበረ።

እርስዋም የተለመደ ተግባርዋን በመከታተል ቤትዋን ስትጠራ ርግና የቤት ዕቃዎችዋን ስታጸዳ ፣ መልአኩ ገብርኤል እንዲህ አበሰራት ፡-

ገብርኤል ፡-

አይዞሽ ማርያም ሆይ ፣ አትደንግጭ አትፍሪ
ጸጋ ተሰጥቶሻል አምላክን አክብሪ ።
ከሴቶቹ ሁሉ አንቺን መርጦአል ጌታ
ኀዘንሽ ይወገድ ልብሽ ይሙላ ደስታ ።

ማርያምም በጣም ደነገጠች ፤ በፍርሃትም እንዲህ ብላ መለሰች፡-

ማርያም ፡-

ምንድር ነው ይህ ነገር የሰላምታ ቃሉ ?
በፍርሃት ተዋጠ ሰውነቴ ሁሉ ።

መልአኩም በሚያረጋጋ ድምፅ እንዲህ አላት ፡-

ገብርኤል ፡-

ከቶ አትሸበሪ ! ምን ያሸብርሻል ?
በእውነት ከእግዚአብሔር ጸጋ ተሰጥቶሻል ።
ከብሮአል ማኅፀንሽ ለመያዝ ወንድ ልጅ
እርሱም መድኃኒት ነው ለዓለም የሚበጅ ።
ስሙንም ኢየሱስ ብለሽ እንድትጠሪው

ማርያም ይህን ነገር በልብሽ አኑሪው ።
የልዑል ልጅ ተብሎ ይህ ታላቅ ይሆናል
የዳዊትም ዙፋን ከአምላክ ይሰጠዋል ።
በያዕቆብ ወገንም ይነግሣል ዘላለም
ኃያል ለመንግሥቱም ፍጻሜ የለውም ።

ማርያም ፡-

ወንድስ እንኳ ሳላውቅ ይህ እንዴት ይሆናል?
ለሚሰማው ሁሉ በጣም ያስገርማል ።

መልአኩም ፍርሃትዋን ለማጥፋት በተሰጣት ጸጋ እያጽናና ይነግራት ጀመር ።

ገብርኤል ፡-

እርግጥ ነው ማርያም በጣም ያስደንቃል
ከቶውን ይህ ነገር ተደርጎ መች ያውቃል ።
ገና መንፈስ ቅዱስ ወዳንቺ ይመጣል
የልዑል ኃይል ደግሞ በላይሽ ይሆናል ።
ካንቺ የሚወለደው ቅዱስ ግሩም ኃያል
የእግዚአብሔር አምላክ ልጅ ተብሎ ይጠራል።
እነሆ ዘመድሽ ኤልሳቤጥ አርጅታ
ታለቅስ ነበረ አንድ ልጅ አጥታ ።
ግን ጕብኝዋ አምላክዋ ኃያል ስለ ሆነ
ልቅሶዋ ቀረና ፍጹም ደስታ ሆነ ።
ይኸው ከፀነሰች ስድስት ወር ሆኖአታል
መካንዋ ኤልሳቤጥ መባልዋ ተረስቶአል ።
ሁሉም ለእግዚአብሔር አይሳንምና
እመኚ ማርያም ሆይ ፣ አሳብሽም ይጽና ።

በዚህን ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ እምነትን ጨመረላት ፤ እርስዋም በእምነት ተሞልታ እንዲህ ብላ መለሰች ፡-

ማርያም ፡-

እነሆ ፣ ባሪያው ነኝ ፤ ታዛዥ ቆሜአለሁ
ያልኸው እስኪፈጸም እጠባበቃለሁ ።

መልአኩ የተሰጠውን ምሥራች ካደረሰ በኋላ ፣ ከእርስዋ ዘንድ ሄደ ። በማርያምም የልዑል ኃይል አደረባት ፤ ከመንፈስ ቅዱስም ፀነሰች ። በዚያም ወራት ተነሥታ ወደ ተራራማው አገር ወደ ይሁዳ ከተማ ፈጥና ለመሄድ አሰበች ።

ማርያም ፡-

ኤልሳቤጥን ሄጄ ጠይቄአት ልመለስ
አይቻት አላውቅም እስከ ዛሬ ድረስ ።

## ፪ኛ ትእይንት

ማርያም ይህን ካለች በኋላ ፣ ለእጮኛዋ ለዮሴፍ ሳትናገር ወደ ዘመድዋ ቤት ሄደች ። ከዘካርያስም ቤት በደረሰች ጊዜ ፣ በደጃፍ ሆና ፡-

ማርያም ፡-

ኤልሳቤጥ ዘመዶ እንደምን ሰነበትሽ ?
በጣም ብትናፍቂኝ መጣሁ ልጠይቅሽ ።

ኤልሳቤጥ የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፣ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ ። በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት ፤ በታላቅ ድምፅም ጮኻ እንዲህ አለች ፡-

ኤልሳቤጥ ፡-

ከሴቶች ተለይተሽ የተባረክሽ ብሩክት
እንዴት ትመጫለሽ አንቺ ወደኔ ቤት ?

የተባረከ ነው የማኅፀንሽ ፍሬ
በመንፈስ ተሞልቶአል ሰውነቴ ዛሬ ።
የሰላምታሽን ድምፅ ስሰማ ቀጥታ
ፅንሱ በሆዴ ውስጥ ዘለለ በደስታ ።
ለምታምን ብሩክት ምስጋና ይገባል
የተነገራት ቃል በርግጥ ይፈጸማል ።

በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ኤልሳቤጥ የተናገረችውን ማርያም በሰማች ጊዜ ፣ ወደ ፈጣሪዋ በተመሰጠ ልብ እንዲህ ብላ ተናገረች ፦

ማርያም ፦

አመስግኚ ነፍሴ ሆይ ፣ እግዚአብሔርን ባርኪ
ስላስታወሰሽም በደስታ እርኪ ።
መንፈሴ ደስ አለው ዳበረ ሕይወቴ
ታላቅ አደረገኝ አምላክ መድኃኒቴ ።
እነሆ ፣ አይቶአልና የባሪያይቱን ውርደት
ያመሰግኑኛል ትውልድ ሁሉም ፍጥረት ።
ቅዱስ ኃያል አምላክ ታላቅ ሥራ ሠርቶአል
ለሚፈሩት ምሕረት ለልጅ ልጅ ይሰጣል ።
ትዕቢተኞች ሁሉ ቀረ አሳባቸው
ብርቱዎች ወረዱ ካስደሳቹ አልጋቸው ።
የተዋረዱትን ከፍ አደረጋቸው
የተራቡትንም በጸጋ ሞላቸው ።
ባለጠጎችንም ከንቱ አደረጋቸው
ትሑታን ጠገቡ ባመኑት ተስፋቸው ።
እግዚአብሔር ባሪያውን ይኸው ተቀበለ
ምሕረቱን አስቦ ወይን ግንድ ተከለ ።
ለደጉ አባታችን እንዳለ ለአብርሃም
አስቦአል ለዘሩም እስከ ዘለዓለም ።

ኤልሳቤጥ መቀመጫ አዘጋጀችላትና ትሕትናን በተሞላ አነጋ ገር እንዲህ አለቻት ፦

ኤልሳቤጥ ፦

እዚህ እወንበር ላይ ድንግል አረፍ በይ
ምግብ ላቅርብልሽ ትንሽ እንድትበይ ።

ማርያም ከተቀመጠች በኋላ ፥ ኤልሳቤጥ እንጀራ አቀረበች ።

ማርያም ፦

ልዑል እግዚአብሔር የፈጠርሽን አምላክ
ስለ ስምህ ብለህ ይህን እንጀራ ባርክ ።

ሁለቱም ምግብ በልተው ሲጨርሱ ፥ ኤልሳቤጥ የምግቡን ዕቃ አነሣችና ለማርያም መኝታ እመደቡ ላይ አነጠፈችላት ።

ኤልሳቤጥ ፦

ካህን ዘካርያስ ጸሎቱን እስኪያደርስ
እኔም እንጀራዬን ጋግሬ ልጨርስ ።
እትልቁ መደብ ተኚ የኔ እመቤት
ተገቢሽ አይደለም ድንግል የጌታ እናት ።
ታላቅ ዙፋን ያለው የኃያላት ኃያል
ከውርደት ሊያከብርሽ ባሪያውን ጐብኝቶአል።
ምስጋና ይድረሰው ላደረገ ይህን

ማርያም ፦

አሜን ።

ማርያምም ሦስት ወር የሚያህል ከእርስዋ ዘንድ ተቀመጠች ። ከዚያም በኋላ ወደ ቤትዋ ለመመለስ አሰበች ።

ማርያም ፦

ብዙ ጊዜ ሆነኝ አንቺ ዘንድ ከመጣሁ
ዛሬስ ወደ ቤቴ መሄድ ፈልጌአለሁ ።

ስለሆነ ጊዜው የሕዝብ ቁጠራ
ቀደም ብዬ ሄጄ እይዛለሁ ተራ ።
በይ ደኅና ሁኚልኝ ኤልሳቤጥ ዘመዴ
አንቺስ እስብሰባው አትመጭም እንዴ ?

ኤልሳቤጥ ፦
ከዘካርያስ ጋር አብረን እንመጣለን
በይ ሂጂ አትቁሚ እንገናኛለን ።
በደኅና ያገናኘን

ማርያም ፦
አሜን ። (———ትወጣለች ።)

# ክፍል ሁለት ።

## ፩ኛ ትእይንት ።

ማርያም ጉዞዋን ወደ እጮኛዋ ቤት አመራች ፤ መፅነስዋም በጉልህ ይታወቅ ነበር ። ወደ ዮሴፍም ስትደርስ ልማዳዊ የሆነ የትሕትና ሰላምታዋን እንዲህ ስትል ታሰማዋለች ።

ማርያም ፡-

ወንድሜ ዮሴፍ ሆይ እንዴት ሰንብተሃል?
ወሬዬን ስታጣ አስበህ ይሆናል ።
መልአክ ተገልጦልኝ ድንቅ ነገር ሰምቼ
ዘመዴ ጋ ሄድሁኝ በድንገት ወጥቼ ።
እርስዋም ኤልሳቤጥ ናት በጣም ያረጀች
ይግረምህ ይድነቅህ ፅንስን ይዛለች ።
ወደ ቤትዋ ስደርስ በውጭ ስነጋገር
ጆሮችዋን አንቅታ ታዳምጠኝ ነበር ።
በበራፉም ሁኜ ስሰጣት ሰላምታ
በእርስዋም ልብ በእኔም ልብ ሞላልን ደስታ ።
ያገኘነው ተስፋ እጅግ ያስገርማል
የአብርሃም አምላክ ሕዝቦቹን ጎብኝቶአል ።
ኤልሳቤጥ ዘመዴም በመንፈስ ተሞልታ
ሰጠችኝ ሰላምታን ምስጋና ለጌታ ።
ጭንቀትህ ይወገድ በል አሁን ደኅና እደር
ቸር ሰላሙን ይስጠን ልዑል እግዚአብሔር ።

ማርያም ተሰናብታ ወደ ቤትዋ ስታመራ ፣ ዮሴፍ የአናጢነት ሥራውን አቁሞ ፤ በሰውነትዋ መለወጥ እየተደነቀ አትኩሮ ይመለከታት ጀመር ። በኋላም እንጨቱን እየጠራረበ የሚከተለውን ተናገረ ።

ዮሴፍ ፡-

በሕዝበ እስራኤል ዘንድ ይህ ነገር ቢሰማ
በጣም አዋራጅ ነው ጽድቅን የሚያሳማ ።
ስለዚህ ልጠብቅ የገዛ ልሳኔን
እግዚአብሔርም ይፍታው ያንን ቃል ኪዳኔን ።
እኔ እርስዋን ለማግባት አጭቻት ነበረ
አሁንስ አየኋት ሰውነቴ አፈረ ።
ጨዋ ንጽሕት ነች ብዬ ስመካባት
ተቃወሰ እምነቴ ምን ጥለት ጣለባት ።
ምንም እንደማያውቅ እንዳላየ ሁኜ
በስውር ልተዋት ነገሩን ሸፍኜ ።
ተግባሬ ሳይከብደኝ አሳብ አታክቶኛል
እስቲ ጋደም ልበል እንቅልፍም ይዞኛል ።

ዮሴፍ ጋደም ይላል ፤ ከባድ እንቅልፍ ይዞት ሳለም ፣ የእግዚ አብሔር መልአክ መጥቶ እንዲህ አለው ።

መልአክ ፡-

የቅዱስ ዳዊት ልጅ ቅኑ ዮሴፍ ሆይ
እኔ የምነግርህን ፈጽም ሳትዘገይ ።
በማይረባ ነገር እርስዋን አትጠርጥራት
ከሴቶቹም ሁሉ በእውነት ንጽሕት ናት ።
ከመንፈስ ቅዱስ ነው የፀነሰችውም
ለመውሰድ አትፍራ አትስጋ በፍጹም ።
ትወልዳለች ሕፃን የሆነ ወንድ ልጅ
እርሱም መድኃኒት ነው ለዓለም የሚበጅ ።
ይህ ታላቅ መድኃኒት ተገልጦ ሲመጣ
ሰይጣን ይሸበራል መድረሻውን ሊያጣ ።
ስሙን ስትሰይምም ኢየሱስ እንድትለው
ዮሴፍ አትዘንጋ ነቅተህ አሰላስለው ።

ዮሴፍም ከእንቅልፉ ነቃና ለትንሽ ጊዜ ሁለት እጁን እጉንጮቹ ላይ በማድረግ ቆየ ። የተነገረውም ከእግዚአብሔር መሆኑን ያለ ጥር ጥር አመነ ።

ዮሴፍ ፡-

ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ የሠራዊት ጌታ
አመሰግንሃለሁ ጥዋትም ሆነ ማታ ።
እጮኛዬን ልተው አስቤ ነበረ
በመጥፎ ምክንያት ልቤ ስላረረ ።
በማላውቀው ነገር ስሠራ ስሕተትን
አስቤ ነበረ ላልሰጥ ምክንያትን ።
እንግዲህ ከሰማሁ ያምላክ ቅዱስ ቃሉን
ተዘጋጅቻለሁ ለመታዘዝ አሁን ።
ጊዜውም ደረሰ የቈጠራው ሰዓት
ማርያም ጋ ሄጄ እንሂድ ልበላት ።

ዮሴፍ ለጉዞ የሚያስፈልጋቸውን ነገር ሁሉ ካዘጋጀ በኋላ ፣ ወደ ማርያም ሄዶ ስትፈትል ያገኛታል ። እንደ ወትሮውም በፍቅር አስተ ያየት ያነጋግራታል ።

ዮሴፍ ፡-

ተነሽና እንሂድ እቈጠራው ስፍራ
ኋላ ሰው ይበዛል አናገኝም ተራ ።
በይ ቶሎ ተነሺ ።

ማርያም ፡-

እሺ ።

በዚያም ወራት ዓለሙ ሁሉ እንዲጻፍ ከአውግስ ጦስ ቄሣር ትእዛዝ ወጥቶ ስለ ነበር ፣ ቄሬኔዎስ በሶ ርያ አገር ገዥ በነበረ ጊዜ ፣ ይህ የመጀመሪያ ጽሕ ፈት ሆነ ። ሁሉም እያንዳንዱ ይጻፍ ዘንድ ወደ

ከተማው ሂደ ። ዮሴፍም ደግሞ ከዳዊት ቤትና ወገን ስለ ነበረ ፣ ከገሊላ ከናዝሬት ከተማ ተነሥቶ ቤተ ልሔም ወደምትባል ወደ ዳዊት ከተማ ወደ ይሁዳ ፣ ከማርያም ጋር ሄደ ። ማርያምም በዚያ በጭንቅ ቦታ ሳለች የመውለጃዋ ጊዜ ስለ ሆነ ፣ በሴቶች የታዘዘው የምጥ ጣር ያዛት ።

ማርያም ፡-

ወንድሜ ዮሴፍ ሆይ ፣ በጣሙን ደከመኝ
ወዴት አረፍ ብዬ ትንሽ እፎይ ባልኩኝ ?

ዮሴፍ ፡-

ብዙ ጫጫታ አለ ሰውም ይገፋሻል
ከዚህ ፈቅ ብንል እንዲያውም ይሻላል ።

ማርያም ፡-

በፍጹም መራመድ አልችልም ወንድሜ
አላበኝ ወበቀኝ ተቀንሶአል አቅሜ ።

ዮሴፍ ፡-

ጥቂት ለመራመድ ከቶውን ባትችይ
እዚህ እበረት ውስጥ ትንሽ አረፍ በይ ።

ዮሴፍ ማርያምን ደግፎ ወደ ከብቶች በረት ከወ ሰዳት በኋላ ፣ እዚያው የበኵር ልጅዋን የዓለምን ኃጢ አት የሚያስወግደውን ጌታችንን ኢየሱስ ክርስቶስን ወለደች ። ማርያምም ልጅዋን በግርግሙ ውስጥ አስተ ኛችው ።

## ፪ኛ ትእይንት ።

በዚያም ምድር መንጋቸውን በሌሊት ሲጠብቁ በሜዳ ያደሩ እረኞች ነበሩ ። የጌታም መልአክ በዙሪያቸው አበራ ፤ እረኞቹም በታላቅ ፍርሃት ተዋጡ ።

፩ኛ እረኛ ፦

ፈራሁ እባካችሁ ልቤ ደነገጠ
ሰውነቴ ሁሉ በፍርሃት ተዋጠ ።

፪ኛ እረኛ ፦

እኔም ፈራሁ በጣም ሆዴ ሁሉ ባባ
ልቤ ተጨነቀ የትኛው ቤት ልግባ ?

፫ኛ እረኛ ፦

ምን እናንተ ብቻ ፈርቻለሁ እኔም
ስጨነቅ ነበረ ተኝቼ በሕልሜም ።
እንሩጥ ፣ እንሩጥ
ከዚህ ካስጨናቂ ልጆች ቶሎ እናምልጥ ።

እረኞቹ በሙሉ ፦

ከዚህ እንነሣ ሁላችን እንሩጥ ።

፬ኛ እረኛ ፦

ለመሮጥ አልችልም ሥሬ ተያይዞአል
ፍጠሩልኝ ዘዴ ልጆች ምን ይሻላል ?

እረኞች በፍርሃት የተሸመደመደውን ጓደኛቸውን አዝለው ለመሄድ ይሞክራሉ ። ነገር ግን ሁሉም በፍርሃት ስለ ተዋጡ ፥ ኃይል አግኝተው ሊይዙት አልቻሉም ። እንደዚያ ሲርመሰመሱ ፥ ድምፅ ከሰማይ ብርሃንና ግርማ ተሞልቶ ይሰማሉ ያያሉም ። ሁሉም ወደቁ ።

መልአኩ ፦

እረኞች አትባቡ ደስታ ይሰማችሁ
ታላቅ የምሥራች እኔ ልንገራችሁ
ዛሬ ተወለደ መድኃኒታችሁ ።
መድኅን ተወለደ በዳዊት ከተማ
ይህን የምሥራች ሕዝቡ ሁሉ ይስማ ።
ምልክትም ደግሞ ይህ ይሁንላችሁ
ሕፃኑን በበረት ታገኙታላችሁ ።
ምስጋና ይድረሰው ለእግዚአብሔር በሰማይ
ሰላም ወርዶአልና ለሕዝብ በምድር ላይ ።

የእረኞች ፍርሃት ጠፍቶ ደስታ በዛላቸው ።

፩ኛ እረኛ ፦

ልጆች ተነሡና ቤተ ልሔም እንሂድ
እግዜር ፈቅዶአልና ብርሃኑን እናይ ዘንድ ።

፪ኛ እረኛ ፦

አሁኑኑ እንሂድ ሁላችን በፍጥነት
እናገኘዋለን በከብቶቹ በረት ።

## ፫ኛ ትእይንት ።

እየተሯሯጡም ወደ ቤተ ልሔም ሄዱ ። ማርያም ንና ዮሴፍን ሕፃኑንም በግርግም ተኝቶ አገኙ ።

፫ኛ እረኛ ፦

አያችሁን ልጆች ከብቶች ከብበውታል
እየተነፈሱም ሙቀት ይሰጡታል ።

፬ኛ እረኛ ፡-

ተራ ሕፃን መስሎ እንዲህ የሚታየው
ለካስ አምላክ ነወይ ሁሉን የሚችለው ?
እጅግ ያስደንቃል ለሚገነዘበው ።

፩ኛ እረኛ ፡—

እናትና ልጁ እንደምን ያምራሉ ?
በእግዚአብሔር ብርሃን ያንጸባርቃሉ ።

፫ኛ እረኛ ፡-

የሆነውን ሳናውቅ ስንፈራ ሳለነ
እግዚአብሔር ይመስገን ክብሩ በራልነ ።

፪ኛ እረኛ ፡-

እንዘምር ልጆች ፥ በአንድነት ሆነን

እረኞች በሙሉ -፡

ምን እያልን ?

፪ኛ እረኛ ፡-

እሰይ አማኑኤል ተወለደ እያልን ።

በሙሉ በዜማ ፡-

ተወለደ አማኑኤል
ተወለደ አማኑኤል
ከድንግል ከድንግል
ተወለደ አማኑኤል ።
ኢየሱስ የዓለም ጌታ
ኢየሱስ የዓለም ጌታ
የዓለም ጌታ ፥ የዓለም ጌታ
የዓለም ጌታ ለእኛ ሰጠን ደስታ ።

እረኞቹ ተንበርክከው ሰገዱለት ፤ ሕፃኑን ከበው ትንሽ ከተመለ ከቱ በኋላ ፣ የሁሉም ልብ ወደየዘመዶቻቸው ሄደው ለመናገር ተቻኰለ።

፫ኛ እረኛ ፦

ሄደን እናውራላቸው ለየቤቶቻችን
በበረት ውስጥ መወለዱን ኢየሱስ ጌታችን ።

፬ኛ እረኛ ፦

አዎን ፣ እውነትህ ነው ይስሙ ይደሰቱ
ኢየሱስን ይዩት እዚህ ከነእናቱ ።

በሙሉ በዜማ ፦

ሕዝቡን ከባርነት ከሰይጣን ሊፈታ
ተወለደ መድኅን የዓለም መከታ ።
በደስታ እንሩጥ ለሁሉም እናውራ
አምላክ ገልጦልናል እጅግ ድንቅ ሥራ ።

በማለት እየዘመሩ ወደየቤተ ሰቦቻቸው ሄደው የሆነውን ነገር ሁሉ ነገሩአቸው ። የሰሙትም ሁሉ ይህን ለማየት ወደ ቤተ ልሔም ይጓዙ ነበር ።

## ክፍል ሦስት ።

### ፩ኛ ትእይንት ።

ሊገረዝም ስምንት ቀን በሞላ ጊዜ ፣ ገና በማኅፀን ሳይፀነስ በመልአኩ እንደ ተባለ ፣ ስሙ ኢየሱስ ተብሎ ተጠራ ። እንደ ሙሴም ሕግ የመንጻታቸው ወራት በተፈጸመ ጊዜ ፣ በጌታ ሕግ ፦ የእናቱን ማኅፀን የሚከፍት ወንድ ሁሉ ለጌታ የተቀደሰ ይባላል ተብሎ እንደ ተጻፈ በጌታ ፊት ሊያቆሙት ፣ በጌታም ሕግ ፦ ሁለት ዋሊያ ወይም ሁለት የርግብ ጫጩቶች እንደተባለ ፣ መሥዋዕት ሊያቀርቡ ወደ ኢየሩሳሌም ወሰዱት ። በዚያም ፣ የእስራኤልን መጽናናት የሚጠባበቅ ስምዖን የሚባል የእግዚአብሔር ሰው ነበረ ። በጌታ የተቀባውን ሕፃን ባየም ጊዜ ፣ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ሕፃኑን አቀፈና እግዚአብሔርን እየባረከ እንዲህ አለ ፡—

ስምዖን ፦

በጸጋህ ጐብኝተህ ነፍሴን ያከበርሃት
ይኸው ሞላ ቃልህ ባሪያህን አሰናብት ።
የሕዝብህን ቤዛ ይህን ታላቅ መድኅን
የማትቀበል ነፍስ እንዴት ትሆን ይሆን ?
ብርሃኑን ሲሰጥ ለአሕዛብ ሁሉ
ይደነቁበታል እስራኤል በሙሉ ።
የሚጠራጠሩም ይሰናከላሉ
በእርሱ የሚያምኑ ግን ፍጹም ይድናሉ ።
በአንቺም ልብ ማርያም ጦር ሰይፍ ይገባል
ሊወድቅም ሊነሣም ልጅሽ ተመድቦአል ።
የብዙዎች አሳብም በእርሱ ይገለጣል

አንዳንዶች ሲያምኑበት ሌሎች ይክዱታል ።
ይህ ለእስራኤል ሕዝብ ለብዙዎቻቸው
መድኅናቸው ሳይሆን ይሆናል መጥፊያቸው።
ሲያነሡ ሲጥሉ ይህ አይሆንም ብለው
ብዙዎች ይወድቃሉ በእርሱ ተሰናክለው ።
ግንበኞች የናቁት የተጠላ ድንጋይ
ማዕዘኑ እርሱ ነው ሁሉን አደላዳይ ።
በዚህ በድንጋይ ላይ የሚሰናከሉ
አንዳቸው ሳይቀሩ ሁሉም ይፈጫሉ ።
ግን ይህንን ዓለት በእምነት ለሚጠጋ
መዳን ብቻ አይደለም ይቀበላል ዋጋ ።
ዕድለ ቢሶቹ ይጠራጠሩታል
ለእኔስ ሞላ ጸጋው ክንዶቼ አቅፈውታል ።
ይህን መድኅን ሳላይ ሞቼ እንዳልቀበር
በመንፈሱ ገልጦ አስረድቶኝ ነበር ።
ጌታ ተቀበለኝ ስሰጥህ ምስጋና
መንፈስ ያስረዳኝን አይቻለሁና ።
ለሰው ሁሉ አስበህ ከጥንት ያቀድኸውን
ምን ቢከብር ባሪያህ ገለጥህለት አሁን ።
አጥንቴ ጅማቴ ኅዋሳቴ ሁሉ
አቅርቡ ምስጋናን ሃሌ ሉያ በሉ ።
እንግዲህ አትፍሪ ነፍሴ ሆይ ክበሪ
የእስራኤል ተስፋ ይመስገን ፈጣሪ ።
ደስ ይበልሽ ነፍሴ አቅርቢ ምስጋና
አሁን ወደ አባትሽ መሄድሽ ነውና ።

## ፪ኛ ትእይንት ።

ከአሴር ወገንም የምትሆን የፋኑኤል ልጅ ሐና የምትባል አንዲት ነቢይት ነበረች ፤ እርስዋም ከድንግ ልናዋ ጀምራ ከባልዋ ጋር ሰባት ዓመት ኖረች ፤ እርስ ዋም ሰማኒያ አራት ዓመት ያህል መበለት ሆና በጣም አርጅታ ነበር ፤ በጾምና በጸሎትም ሌሊትና ቀን እያ ገለገለች ከመቅደስ አትለይም ነበር ። በመንፈስ ቅዱስ ተሞልታ ስለ ኢየሱስ እንዲህ ተናገረች ፦

ሐና ነቢይት ፦

የሠራዊት አምላክ የነገሥታት ንጉሥ
ሕያው ብፁዕ ስምህ ይባረክ ይቀደስ ።
በነቢያትህ አፍ የተናገርከውን
ደስታችን በዛ ስለ ፈጸምህልን ።
የሠራዊት አምላክ የሠራዊት ጌታ
የታሰረውን ሕዝብ ከግዞት ልትፈታ
ላክህልን መድኃኒት ላክህልን ጠበቃ
ደስታችን ይመለስ ኀዘናችን ይብቃ ።
ጠላታችን ሰይጣን ፎክሮ ነበረ
ነገር ግን ዓላማው ተበላሽ ቀረ ።
ማርያም ልጅሽን ያገኘ ሂጂ በደስታ
የታሰረው ሁሉ በነጻ ተፈታ ።
ሃሌ ሉያ ፣ ሃሌ ሉያ ።

# ክፍል አራት ።

## ፩ኛ ትእይንት ።

ኢየሱስም በተወለደ ጊዜ ፣ ሰብአ ሰገል ለተወለ ደው ሕፃን ገጸ በረከት ሊያቀርቡለት እየጠየቁ በኮ ከብ መሪነት ከምሥራቅ ተነሥተው ጉዞ ጀመሩ ። ከዚያም ወደ ንጉሥ ሄሮድስ ቤት ሄደው መጠየቅ ግድ ሆነባቸው ።

ንጉሥ ሄሮድስ መጽሐፍ እያገላበጠ ሲያነብ ፣ ዘበኛ ይገባል ።

ዘበኛ ፦

ከምሥራቅ የመጡ ብዙ ሰዎች ሆነው
እውጭ ቆመዋል ንገሩልን ብለው ።

ሄሮድስ ፦

ታዲያ ፣ እስካሁን ለምን አቆምሃቸው ?
በል አሁን ሂድና በቶሎ አስገባቸው ።

ሰብአ ሰገል በትሕትና ለንጉሡ እጅ ከነሡ በኋላ ይቆማሉ ። ሄሮድስም በእጅ እንዲቀመጡ ፣ ምልክት ከሰጣቸው በኋላ ይቀመ ጣሉ ።

ሄሮድስ ፦

የመጣችሁበት ጉዳዩ ምንድር ነው ?
አስረዱኝ በቶሎ ወደ ውጭ ልሄድ ነው ።

፩ኛ ጠቢብ ፦

ከምሥራቅ ወደዚህ መጥተናል በሩጫ
እየተከተልን የኮከብ አቅጣጫ ።

ሄሮድስ ፦

በኮከብ መሪነት የመጣችሁበት
ጉዳዩን ልወቀው እስቲ አስረዱኝ በእውነት ።

፪ኛ ጠቢብ ፦

የአይሁድ ንጉሥ የተወለደው የት ነው ?
ልንሰግድለት ነበር እኛ የመጣነው ።

ሄሮድስም የአይሁድ ንጉሥ ስላሉ ፣ በጣም ደነገጠና ንዴቱን በተቻለው መጠን ለመሸፈን ሞከሮ እንዲህ አለ ፦

ሄሮድስ ፦

ከሕዝቡ ጠይቄ እስከምነግራችሁ
እረፉ እዚያ ክፍል በአንድነት ሆናችሁ ።

ይወጣሉ ።

ወደ ዘበኛው ዞሮ ፦

አንተ አሽከር ፣ትእዛዜን አድምጥ ነቅተህ በጥሞና
የካህናትን አለቆች ጥራቸው ሂድና ።
የሕዝቡንም ጸፎች በሙሉ ጥራቸው
ሁሉም ይሰብሰቡ እንድጠይቃቸው ።

ዘበኛ ፦

እሺ የኔ ጌታ
እነግራቸዋለሁ ትእዛዝዎን በደስታ ።

ዘበኛው ከወጣ በኋላ ፣ ሄሮድስ ብቻውን በንዴት ተቃጥሎ የሚያደርገውን ያሰላስል ነበር ። እንደ እብድም ብቻውን ያወራ ነበር ።

ሄሮድስ ፦

አዋቂዎችን ሁሉ ሰብስቤ በአንድነት
ተወልዶ እንደሆነ ይኸ ሕፃን በእውነት
መረዳት አለብኝ ለመንግሥቴ ጽናት ።

አይወርስም አልጋዬን በሕይወት እያለሁ
መጀመሪያ የእርሱን ነፍስ እኔ እሠዋታለሁ ።
መንግሥቴ ከእኔ ጋር ትኖራለች እንጂ
ማንም አይወስዳትም ፈልቅቆ ከእኔ እጅ ።
"የት ነው የአይሁድ ንጉሥ?" ሲሉ ማውራታ
ቸው
ከቶ ምን መስዬ እኔ ታየሁአቸው ?
ሥልጣናዊ ቃሌን አሁን እሰጣለሁ
ሕፃናትን ሁሉ ጨርሼ አስፈጃለሁ ።

ሄሮድስ በሁለት እጁ ጉንጩን ይዞ አንገቱን ወደ መሬት አቀር ቅሮ ሲተክዝ ዘበኛ ይገባል ።

ዘበኛ ፡-

ንጉሥ ሆይ ፥
የተጠሩት ሁሉ መጥተው እደጅ ናቸው ።

ሄሮድስ ፡-

በል ፈጠን በልና በቶሎ አስገባቸው ።

የተጠሩት የካህናት አለቆች ፥ የሕዝብ ጸሐፊዎችና አዋቂዎች ገብተው እንደ ቆሙ ፥ ሄሮድስ በእጁ እንዲቀመጡ ካሳያቸው በኋላ፥ በጸጥታ ይቀመጣሉ ። በቀጥ ፡-

ሄሮድስ ፡-

እናንተ ሁላችሁ ከዚህ ያላችሁት
ኢየሱስ ወዴት ነው የሚወለድበት ?
እንድታስረዱኝ ነው የተጠራችሁት
መልስ እጠብቃለሁ ከእናንት ለመረዳት ።

፩ኛ ካህን ፡-

ንጉሥ ሆይ ፡-
በቤተ ልሔም ውስጥ በእርግጥ ይወለዳል
በነቢይ ተነግሮ በመጽሐፍ ተጽፎአል ።

፪ኛ አዋቂ ፦

የይሁዳ ምድር አንቺ ቤተ ልሔም
ከአይሁድ አለቆች ከቶውን አታንሽም ።

ወደ ሄሮድስ ዘወር ብሎ ፦

አዎ ፣ ከሁሉ አስቀድሞ ተመስክሮለታል
አሁንም ኢየሱስ እዚያው ይወለዳል ።

፫ኛ ጸሐፊ ፦

በቤተ ልሔም ውስጥ መስፍን ይወለዳል
ሕዝበ እስራኤልም ይጠባበቁታል ።
ዘመኑም አሁን ነው የሚወለድበት
ንጉሥ አይጠርጥሩ ፣ ይመኑ በእውነት ።

ሄሮድስ በንዴት ፦

በእርግጥ ይኸ መስፍን ተወልዶ እንደሆነም
ይገደላል እንጂ በሕይወት አይኖርም ።
አምናለሁ መንግሥቴ ከእጄ እንደማትወጣ
ይደርሰዋል በእኔ እጅ ክፉ የሞት ዕጣ ።
በዙፋን ተቀምጦ ሳይሠራበት ገና
ንጉሥ ነው በመባል አተረፈ ዝና ።

፪ኛ አዋቂ ፦

ብዙ አይናደዱ ንጉሥ አይቈጡ
የሚያደርጉትንም ያስቡ በቅጡ ።
ሕፃኑን ለመግደል ልብዎ ቢያስብም
እርሱን ከሕዝብ መኻል ሊለዩት አይችሉም።

ሄሮድስ ፦

መለየትም ባልችል እርሱን ከሕዝብ ሁሉ (በቍጣ)
ሕፃናት በሙሉ በሰይፍ ያልቃሉ ።
የማንም ሕፃን ደም ቢፈስ ግድ የለኝም

ከመንግሥቴ ለእኔ ሰው አይበልጥብኝም ።
ከሁለት ዓመት በታች የሆነ ዕድሜአቸው
ሕፃናት በሙሉ መሞት አለባቸው ።
ልቦናዬ አይራራም ጨካኝ ነው መንፈሴ
ለሰው አላስብም አብልጩ ከራሴ ።

፫ኛ ጸሐፊ ፡-
ጭንቀትዎ እንደዚህ ከቶ ለምን በዛ ?
ወደ እብደት ይወስዳል መናደድ ሲበዛ ።

፩ኛ ካህን ፡-
አዎን ፥ በመጠኑ ቢያደርጉት መልካም ነው
በአሁኑ አያያዝስ ለጤናዎ አስጊ ነው ።

ሄሮድስ ፡-(ራሱን እያወዛወዘ)
ግድ የለም ሂዱልኝ አሁን እቤታችሁ
እናንተም ፈልጉት በየበኩላችሁ ።

የተጠሩት እንግዶች ሁሉ ከሄሮድስ ቊጣ የተነሣ በጣም ስለ ደነገጡ ፥ በጸጥታ ወጡ ። ሄሮድስም ብቻውን በንዴት እንዲህ እያለ ይናገር ነበር ።

ሄሮድስ ፡-
አዎ ፥ ይህንን ንዴቴን በደስታ ለውጬ
እንግዶችን ልጠይቅ በፍቅር ተውጬ ።
ከገለጡልኝም መጀመሪያ እነርሱ
ሕፃኑን አይተውት ደርሰው ይመለሱ ።
ከዚያ በኋላ ግን እኔ መላ አውቃለሁ
የማየው መስዬ ገድዬ እመጣለሁ ።
አዎን ፥ ይህ አሳብ ነው እኔን የሚያዋጣኝ
ዘበኛ ፥ ዘበኛ ፡- (———ይገባል ።)
እነዚያን እንግዶች ወደዚህ ጥራልኝ ።

ዘበኛ ፡-

 እሺ ፤ ንጉሥ ሆይ ፤
ትእዛዝዎን በደስታ እፈጽማለሁኝ ።

ሰብአ ሰገል እጅ ነሥተው ከተቀመጡ በኋላ ፤ ሄሮድስ ንዴቱን በመሸፈን በለሰለሰ አነጋገር ፡-

ሄሮድስ ፡-

ወደ ቤተ ልሔም መንገዳችሁን አምሩ
ስለ ተወለደው ሕፃን ግን መርምሩ ።
ካገኛችሁትም በዚህ ተመለሱ
እኔም እዚያው ሄጄ እንድሰግድ ለእርሱ ።
ቤተ ልሄም ላለው ላስደናቂው ሕፃን
ሄጄ እንዳበረክት ወርቅ ከርቤና ዕጣን ።
ፈልጌአለሁና ይህን እንዳትረሱ
እርሱን ካገኛችሁ እኔ ዘንድ ድረሱ ።

፩ኛ ጠቢብ ፡-

እናመሰግናለን እግዚአብሔር ይስጥልን
ስላደከምንዎ ይቅርታ ያድርጉልን ።

ሄሮድስ ፡-

የእናንት ብቻ አይደለም የኔም ተግባሬ ነው
ሕፃኑን ለማየት በጣም ፈቃዴ ነው ።
በሰላም ያገናኘን ።

ጠቢባኑ ፡-

አሜን ።

ሰብአ ሰገል እጅ ነሥተው እየተደሰቱ ጉዞአቸውን ለመጀመር ከቤተ መንግሥቱ ወጡ ። ሄሮድስ ወደ በሩ እየተመለከተ እንዲህ እያለ ዛተ ።

ሄሮድስ ፡-

አዎ ፣ ያገናኘን እጠባበቃለሁ
ለኢየሱስ ዋጋውን እኔ እሰጠዋለሁ ።
እርሱ ብሎ መስፍን ዝና እስከዚህ ድረስ
እናያለን እስቲ በዚህ ዓለም ሲነግሥ ።
በኔ በሄሮድስ እጅ ይፈሳል የእርሱ ደም
በሕይወቴ እያለሁ መንግሥቴን አይወስድም።
እኔ ሄሮድስ ነኝ የጀግኖቹ ጀግና
ማን ያልሰማ አለ የታሪኬን ዝና ።
የሰገል ሰዎች ግን ሞኞች ስለ ሆኑ
በትንሹ ሕፃን በየሱስ አመኑ ።
ወይኔ ሄሮድስ የነገሥታት ንጉሥ
እንቅልፍ አይወስደኝም የእርሱን ደም ሳላፈስ ።
በድንገት ብስጭት ተቃጠለ ልቤ
ሳላገኘው አልቀር እንዲህ ተንገብግቤ ።
የነደደው ልቤ ፍሙ የሚበርደው
ኢየሱስን ይዤ በሰይፍ ሳርድ ነው ።
አይቀርም መያዜ አይቀርም መግደሌ
ጨካኝ ነው መንፈሴ ፣ ጨካኝ ነው አመሌ ።
እህ ወይ እኔ ! ወይ እኔ !
ተቀሰቀሰብኝ የጀግንነት ወኔ ።
ትኩሣቴ በዛ ልተኛ አልጋ ላይ ።
መቼም ካልገደልሁት አላርፍም ከሥቃይ ፤
እፎይ — — — እፎይ — — — እፎይ ።

ሄሮድስ በእጁ ልቡን ደግፎ ወደ መኝታ ቤቱ ይሄዳል ።

## ፪ኛ ትእይንት ።

ሰብአ ሰገል የቤተ ልሔምን መንገድ ይዘው ሲሄዱ ፣ በናፍቆት ተውጠው እንዲህ ይዘምሩ ነበር ፦

ሰብአ ሰገል ፦

ምን ይሆናል ለሰማይ መናኝ
ድኖ ካምላክ ጋራ ሲገናኝ ።
ምን ያህል ደስታ አለ በላይ
በቤቱ በሰማይ ።

በድንገት ኮከቡ ታያቸውና እንደ ቀድሞው በብርሃኑ ሕፃኑ የሚገኝበትን አቅጣጫ አሳያቸው ።

፩ኛ ጠቢብ ፦

ተመስገን አምላክ ሆይ ፣ ይድረስህ ምስጋና
ኮከቡ ብርሃኑን ሰጠን እንደገና ።

፪ኛ ጠቢብ ፦

ኮከብ ባይታየን ብርሃን ባይሰጠን
ከንቱ እንቀር ነበር ወድቀን ተንከታክተን ።

፫ኛ ጠቢብ ፦

ተመስገን ስንለው አምላክ ይደሰታል
ሌላው ነገርማ ሞልቶታል ተርፎታል ።

ሰብአ ሰገል ከምሥራቅ ያዩት ኮከብ ሕፃኑ ባለበት ቦታ ላይ ብርሃኑን ስለ ዘረጋ ፣ ወደ ቤት ገቡ ፣ ሕፃኑንም ከእናቱ ከማርያም ጋር ሲያዩት ወድቀው ሰገዱለት ። ሳጥኖቻቸውንም ከፍተው እጅ መንሻ ወርቅ ፣ ዕጣንና ከርቤም አቀረቡለትና እንደ ተንበረከኩ ፦

፩ኛ ጠቢብ ፡-
ሰላም ላንተ ይሁን ይድረስህ ምስጋና
ለእኛ አዲስ ሕይወት ሰጥተኸናልና ።

በአንድነት ፡-
ሃሌ ሉያ
ሃሌ ሉያ ።

፪ኛ ጠቢብ ፡-
የልዑል ልጅ አንተ ቅዱስ ክቡር ኃያል
ምስጋና ይድረስህ ደስታ ተሰምቶናል ።

በአንድነት ፡-
አሜን
አሜን ።

ከተንበረከኩበት ተነሥተው ፡-

፫ኛ ጠቢብ ፡-
የነገሥታት ንጉሥ የደካሞች ዋልታ
የድውያን ጤና ተወለደ ጌታ ።
የነገሥታት ንጉሥ የተወለደበት
ይባረክ ይኸ ቀን ይባረክ ይኸ ዓመት ።

በአንድነት ፡-
ይባረክ ይኸ ዓመት ።

፩ኛ ጠቢብ ፡-
የተባረክሽ ብሩክት ጸጋ የሞላብሽ
ከሴቶች ሁሉ አንቺ ኧረ እንዴት ተመረጥሽ ?
ድንግል ቅድስት ክብርት ደግሞም ብፅዕት ነሽ
ከእግዚአብሔር ተልኮ መልአክ አበሠረሽ ።

በአንቺ የመጣልን መድኃኒታችን
እኛን ለመምራት ነው ወደ ፈጣሪያችን ።
ምን እንመልሳለን ለዚህ ክብር ውለታ
እናቅርብ ምስጋና ከጥዋት እስከ ማታ ።

በሙሉ ፦

አሜን ።

ሰብአ ሰገል ከተቀመጡ በኋላ ፣ ትንሽ የአእምሮ ጸሎት ሲያደርሱ ፣ የእግዚአብሔር መልአክ ይናገራቸዋል ።

መልአኩ ፦

ወደ ሄሮድስ ቤት እንዳትመለሱ
ሕፃኑን ለመግደል አስቦአል መንፈሱ ።
አይችልም ለመግደል ቢፈልግም ሆዱ
ግን እናንተ በፍጹም ወደ እርሱ እንዳትሄዱ ።

እርስ በርሳቸውም ተያዩ እግዚአብሔር ስለ ገለጠላቸውም ነገር ተደነቁ ።

፩ኛ ጠቢብ ፦

እንግዲህ ቀጥታ በዚህኛው መንገድ
ወደ አገራችን ዝም ብለን እንሂድ

፪ኛ ጠቢብ ፦

ሄሮድስ ተንኰለኛ ልቡ የከረረ
እኛን ሊያሳስተን አስቦ ነበረ ።

፫ኛ ጠቢብ ፦

ሄሮድስ ሲያታልለን ሠውሮ ተንኰሉን
አምላክ በመልአኩ መራን ቅን መንገዱን ።
ሄጄ እንድሰግድለት ፈቃዴ ነው ያለው
ለመግደል ነበረ ለካ እርሱ ያሰበው ?

፩ኛ ጠቢብ ፦

እርሱ ፈለገ እንጂ ፈጻሚው ማን ሆነ ?
ያቀደው አሳቡ እንደ ጢስ በነነ ።

፪ኛ ጠቢብ ፦

በሉ እየዘመርን እንሂድ ሀገራችን
ሰምተው ይደሰቱ ቤተ ሰቦቻችን ።

በዜማ አንድነት ፦

አንድ ነገር በልቤ ሆነ ኢየሱስ ሲያድነኝ
እርግማኔ ሁሉ ተሻረ ነፃነትን አገኘሁኝ ።
ሕይወቴም በፍቅር ጋለ ክብር ክብር ለስሙ
የነፃነት ልደት ታወጀ ያላወቁ ሁሉ ይስሙ ።

በታላቅ ደስታ ተውጠው በመዘመር እግዚአብሔርን እያከበሩ ወደ ሀገራቸው ተመለሱ ።

## የአዘጋጁ አስተያየት

አድማጩ ተገንዘብ ፣ አንባቢው አስተውል
የአምላክ ልጅ ቤት አጥቶ ሲንከራተት ሲውል ።
ዓለም በአዳም ጥፋት ስለ ተረገመች
መድኃኒት ቢመጣ አልቀበል አለች ።
የኢየሱስ ዝና ቢበርቅ ከጨለማ
አልወደደም ሄሮድስ በፍጹም ሊሰማ ።
ሄሮድስ ብቻ አይደለም መድኃኒቱን ያጣ
ዛሬም በእኛ ዘመን አለ ይኸው ጣጣ ።
እምነን ለመናዘዝ መንገዱ ጠፍቶብን
የምናሳዝነው ብዙ ፍጡር አለን ።
እውነትም መንገድም እኔ ነኝ እያለ ።
ይህንን በመግለጥ ጉባኤ ላይ ዋለ ።
ማንም ሰው አይችልም ማግኘት ሌላ መንገድ
ቀጥታው እርሱ ነው ወደ ኢየሱስ እንሂድ ።
መልካሙ እረኛችን እርሱ ስለ ሆነ
በደንብ ይሰማራል በየሱስ ያመነ ።
ከእረኛም እረኛ የማያንቀላፋ
በየሱስ ያመነ አለው ታላቅ ተስፋ ።
ጊዜ ያልፋል ሀብትም ሁሉም ይጠፋሉ
ግን በቸሩ እረኛ በክርስቶስ ያሉ
ዛሬም ለዘላለም ሁሌ ይኖራሉ ።
የመጣው ቢመጣ የሚያስፈራ ነገር
እረኛው ጋሻ ነው አለው ታላቅ ፍቅር ።
ነፍሱን አሳልፎ እስከ መስጠት ድረስ
ይወዳል በጎቹን ርኅሩኁ ኢየሱስ ።
በጎቹን ያፈቅራል አብልጦ ከራሱ

ተናግሮታልና እርሱ በምላሱ ።
መልካም እረኛ ነኝ በጎቼን ጠባቂ ።
ላድን እችላለሁ ከተኩላ ነጣቂ
ቢበዛም ጠላቱ በዚህ ጨለማ ዓለም
በጎቼን ከእጇ የሚነጥቀኝ የለም ።
የሚል ታላቅ ተስፋ ትቶአል ለበጎቹ
በተስፋው በማመን በዝተዋል መንጎቹ ።
ከዚህ ከታመነ ከአምላካዊ ጸጋ
ሁላችን እንውሰድ በሩ ሳይዘጋ ።
አንድ ቀን ይዘጋል የአምላክ ጽኑ በሩ
አንባቢ ፤ አድማጮች ቶሎ ተመከሩ ።
ይህ ጊዜ ጥሩ ነው ይህ ሰዓት ጥሩ ነው
የምሕረት የጸጋ የፍቅር ጊዜ ነው
በሩ ሳይዘጋ ቶሎ መሻማት ነው ።
የነፍሳችን አዳኝ የሱስ የከበርከው
ግባ በልቤ ውስጥ ሕይወቴንም ባርከው ።
አንተም ተቀበለው የሱስን ቻላ አትበል
ስትሠቃይ አትኑር በዓለም ማዕበል ።
ድንገት ጣዕረ ሞት በአልጋ ላይ ሲይዘን
የያኔው ኑዛዜ አይችልም ሊያድነን ።
ዘመዶቼ እንግዲህ ዛሬ ነገ አንበል
በዚችው ደቂቃ ጌታን እንቀበል ።

አሜን ።

ጥሩነሽ ይመር ።

ፕሬስብቴሪያን ሥነ ጽሑፍ ድርጅት ።

AP—19—G

$ 0.50

ሴንትራል ፡ ማተሚያ ፡ ቤት ።